# እውነት መንፈሳዊ ጋዜጣ



# ርዕሰ አንቀጽ

## እንዴት ዝም ለማለት ቻልን ?

ከዘለዓለም ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያዘጋጀውን ኢየሱስ ክርስቶስን ዘመኑ በደረሰ ጊዜ ወደ ምድር በመላክ የሚወደውን አንዲያ ልጁን በመስቀል ላይ እንዲሞት በመፍቀድ አሳልፎ በመስጠት ፍቅሩን ገለጠ፤ ልጁም ኢየሱስ ክርስቶስ ህይወቱን በመሰዋት ቤዛ ሆኖ ሞታችንን በሞቱ ሽሮ እዳችንን ከፈለው፤ እግዚአብሔር በኃጢያት ባህር ያለውን የሰውን ልጅ ያድን ዘንድ ማድረግ የሚገባውን ሁሉ አድርጓል። የተከፈለው ዋጋ የሰውን ልጅ ሁሉ ማዳን የሚችል ቢሆንም እንኳን ይህን እድል ያገኙ የዚህ መዳን እውቀት በርቶላቸው ከዚህ የህይወት ውኃ ምንጭ ጠጥተው የረኩ እጅግ ጥቂቶች ናቸው።

እኛ የመዳን እውቀት የበራልን ወደ እረፍቱ የገባን የወንጌል እውነት ገብቶን ወደ ነፍሳችን እረኛ በመመለስ ከመቅበዝበዝ የዳንን የምሥራቹን ይዘን እንዴት ዝም ማለት ቻልን ? <u>እስቲ ሰውን ያለክርስቶስ እንየው እንዴት ያሳዝናል</u> ለሲኦል የተመደበ በጨለማው ሥልጣን ሥር የወደቀ በኃጢያት ሰንሰለት የታሰረ የእግዚአብሔር ፍርድና ቁጣ በላዩ ላይ ያለ ለዘለዓለም እድሉ የተበላሸበት፤ሆኖ ሳለ እኛ የሕይወትን የመዳን አመልካች መልህክት በእጃችን እያለ በተጨማሪ ሰውን ከእግዝያብሔር ጋር ለማስታረቅ አደራውን ተቀበይ ሆነን ነገር ግን እንዴት ዝም ማለት ቻለን? የቀደሙ አባቶቻችን እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም አሉ እኛስ??

የሐዎ -ሥራ 4፤19

የቤተ/ክርስቲያኒቷ መልዕክት



# በውስጥ ገጾች


<u>ዕርሰ አንቀጽ፤</u>
እቲ ሰውን ያለክርስቶስ እንየው እን ዴት ያሳዝናል!

<u>ዝም በሉ፤</u>
ያኔ በእርሻው ስፍራ እያለ መጎናጸፊያውን ሲጥልበት በሬውን ሞፈር ቀንበሩን ያስጣለው መለኮታዊ ጥሪ ከፍ ብሎ ተስሏል ስለዚህ ከጉዞው ወደ ኋላ ሊያስቀረው አልቻለም።

<u>ከሴቶች ለሴቶች፤</u>
ወደ ተጣለው ሕፃን የንጉስ ልጅ እንድትመጣ እንድታየው እና እንታነሳው የልዑል አምላክ ፈቃድ ሆነ፤

<u>የመንገድ ስንቅ፤</u>
ዓለምን ለማሸነፍ አትታገል ለእግዚአብሔር ተሸነፍ ዓለምን ታሸንፋለህ፤

<u>ስሜ አልለይሽም</u>
ጉዳትሽ ገብቶኛል እኔንም ነክቶኛል
ባሌን በማጣቴ ውስጤ ተረብሾል

አይኖቼም አዩና
ግርማ ሞገስ በጎ ቸርነትን
አሉ አዎን አዎን
ወግማህረግመጣልን


ቦስተን የምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ/ክርስቲያን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ የምታምን የክርስቶስ ኢየሱስን የማዳን ወንጌል ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ የምታሰራጭ ቤ/ክ ነች። ይህም ጋዜጣ ወንጌልን ከምታሰራጭባቸው መንገዶች አንዱ ሲሆን በቤ/ክ የሥነ-ጽሁፍ አገልግሎት አባላት እየተዘጋጀ በየሁለት ወር አንድ ጊዜ ይቀርባል።


የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ
ፖስተር ምሕረቱ ሌጀቦ
Email Meheretu2614@Yahoo.com
Telephone 617-792-5764

ዋና አዘጋጅ............... ሄኖክ ተሾመ
ምክትል አዘጋጅ.......ሐብታሙ አስረስ
የውብዳር ፍሰሐ
ኮምፒዩተር ጽሁፍ.....ትርሲት ጥላሁን
የፊት ገጽ ዲዛይነር.......ዝግጅት ክፍሉ


ለቀጣዩ እትም ይረዳ ዘንድ የእናንተ ተሳትፎ ወሳኝ ሚና ስላለው በሚቀጥለው አድራሻ ያላችሁን አስተያየትና ጥያቄ ላኩልን፡አድራሻ


Ethiopian Evangelical Church in Boston
88 Tremont StreetBoston, MA 02108
Tel. 617-816-8827


## የአንባቢያን አስተያየት ፡

*በጌታ ፍቅር የተወደዳችሁ ቅዱሳን ወንድሞችና እና እህቶች በሥነ ጽሁፍ ውስጥ የምታገለግሉ በሙሉ እንደምን ናችሁ የጌታ ሰላምና ፀጋ ይብዛላችሁ በዚህ አገልግሎት ውስጥ ስትጋደሉ ተስፋ ባለመቁረጥ እንድትተጉ አበረታታችኋለው ከዚህ በኋላ ጌታ ቢፈቅድ ከእናንተ ጋር በሥራችሁ ለመተጋገዝ ልቤን አዘጋጅቼአለሁ፤ ጌታ ኢየሱስ እንደረዳኝ መጠን ከእናንተ ጋር ለመሥራት እተጋለሁ ጌታ ኢየሱስ አብዝቶ ይባርካችሁ።*

**እህታችሁ ፀጋ አለማየሁ፤**

*ከሁሉ አስቀድሜ በዘመናት ሁሉ መሃከል በሥራ ላይ የሆነውን ታላቁን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ይህንን አስተያየት እንድጽፍ ያስገደደኝ በወንድም ሔኖክ ተሾመ የተጻፈው ዝም በሉ ! የሚለው መልእክት ባነበብኩበት ሰዓት ነው አስታውሳለሁ ወደሥራ እየሄድኩኝ በባስ ውስጥ ሆኜ እውነት ቁጥር 8 ጋዜጣ ከቦርሳዬ አውጥቼ ማንበብ ጀመርኩ ዝም በሉ በሚለው ርዕስ ሥር ያለውን መልእክት ገና ከመጀመሬ አይኖቼ በእንባ ተሞሉ ለገባኝና ላደረገው ለወሰንኩት መንፈሣዊ እውነት የገባሁትን ቃል ኪዳን አስታወሰኝ፤ እኔ ጋር መልእክቱ <u>ሬማ የጊዜው ቃል</u> ሆነልኝ በውስጤ ያለውን <u>የተዳፈነው እሣት እንደመጫር</u> ሆኖ ነው የደረሰኝ።* **<<በዚህ ዘመን ያላችሁ እውነተኛ ባለ እርዕዮች ሰማያዊ ተልእኮና ጥሪ ያላችሁ ማቄን ጨርቄን ሳትሉ ለሰማችሁት እውነት ለተቀበላችሁት መለኮታዊ አደራ እራሳችሁን ለሰዋችሁ ሁሉ>>።** *ከመልእክቱ የወሰድኩት ቃል ሲሆን መልክቱ በሙሉ ሃይል ያለው Powerful እና Onetime massage የጊዜው የእግዚአብሔር መልእክት አድርጌ ለራሴ ወስጄዋለሁ።ያላነበባችሁ ይህን መልእክት እንድታነቡት በዚህ አጋጣሚ ልገፋፋችሁ እወዳለሁ፤ ወንድም ሔኖክ ተሾመንና ቤተሰቡን እንዲሁም የእውነት ጋዜጣ አዘጋጆች በሙሉእግዚአብሔርይባርክእላለሁ።*

**ሳባ አዳሙ**

*ውድ እህታችን ፀጋ አለማየሁ እና ውድ እህታችን ሣባ አዳሙ የጌታ ሰልምና ፀጋ ይብዛላችሁ ስለሰጣችሁን ገንቢ አስተያየት ጌታ ይባርካችሁ ተሳትፎችሁ አይለየን።*

**ዝግጅትክፍሉ**

# ከሴቶች-ለሴቶች

## አስተዋይ እናት ፤

እናትነት ከእግዚያብሔር የሚሰጥ ክብር ማእረግም ነው። ማንም ከመሬት ተነስቶ እናት ሊሆን አይችልም። ገና ከማህጸን ጀምሮ የጠበቀ የነፍሥ ትስስር ያለበት የህይወት ትዳና። እናትነት ሲባል በሰው ሁሉ አእምሮ ውስጥ አንድ ነገር ብልጭ ይላል የዘጠኝ ወር የማህጸን ቆይታ አጥንት ከአጥንት ሲጋጠም ጅማት ሲዘረጋበት ቆዳ ሲለብስ የሰውነት አካሉ በሂደት ሙሉ ሲሆን.. ይህ ሁሉ በእናት ማህጸን ይህን ትስስር ታድያ ማን ሊበጥሰው? ማንስ ሊፈታው? ይገርማል!!

እግዚአብሔር እንኳን ከሕዝብ ጋር ስላለው የማይሻር አንድነት ሲናገር እናትነትን ነበር ምሳሌ ያደረገው እንዲህ ሲል እናት ልጇን ትረሳ ዘንድ ይቻላል ወይ? እራሱ ሲመልሰው እናት ትረሳ ይሆናል አለ። በእርግጠኝነት ትረሳለች አላለም። ልብ በሉ የእናትና የልጅ ትስስር..... በአንድ ወቅት የመጻአተኞች መብዛት ያሰጋው አንድ ጨካኝ ንጉሥ አስደንጋጭ አዋጅ አወጣ ወንድ ልጅ ሲወሰድ አውጥታችሁ ወንዝ ጣሉ ባትጥሉት ግን .... ዘፀ 2፡22 አቤት ጭካኔ የእናትና የልጅን የነፍሥና የደም ትሥሥር መች የሞት አዋጅ ሊበጥሰው፤ ታዲያ በዚህ ወቅት ስለ ልጇ የጨከነች አንዲት ብልህ ሴት ተገኘች የሙሴ እናት በፍጹም ልጄ አይሞትም ብላ ከሞት ጋር ተፋጠጠች የንጉስ አዋጅ ሻረች 3 ወር። ዕብ 11፡23 ነገሩ እየገፋ ሲመጣ መጥተው አይደ እያየ ልጇን እንዳይገድሉባት አንድ ብልሃት ፈጠረች የደንገል ሣጥን ወስዳ ዝፍትና ቅጥራን ለቀለቀችው ህፃኑንም አኖረችበት ዘፀ 2፡23 የደንገል ሣጥን የሚሰራበት እንጨት በውሃ ላይ የሚንሣፈፍና ግብጻውያን በዛን ጊዜ ለጀልባ የሚጠቀሙበት ነው የሙሴ እናትም ለትንሹ ህፃን በልኩ ጀልባ ሰርታ ውኃ ዳር ጣለችው ምን አልባት እንኳን ከየት መጣ የሚል የንጉስ ጥያቄ ቢመጣ ልትጋፈጥ ወስና። ሆኖም እግዚአብሔር አብሯት ነበርና በልጇም ላይ ከነበረው አላማ የተነሣ እሱም ተረፈ እናቱም ከንጉስ ቁጣ አመለጠች። ይህ በእንዲህ እንዳለ የዚች አስተዋይ እናት ውጤት የሆነችው ልጇ በባህር የተጣለውን ብላቴና በሚደንቅ መንገድ ተመልሶ ወደ እናቱ እቅፍ እንዲገባ ግሩም የሆነ ጥበብ ተጠቀመች ወደ ተጣለው ሕፃን የንጉሱ ልጅ እንድትመጣ እንድታየውና እንድታነሳው የልኡል አምላክ ፈቃድ ሆነ። በዚህን ጊዜ ነበር የብላቴናው እናት አንድ ጥያቄ ለንጉስ ልጅ ያቀረበችው የሚያጠባልሽ ሞግዚት ትፈልጊያለሽ ወይ? ጥያቄዋም በንጉስ ልጅ ፊት ተቀባይነት አገኘ ህፃኑም በእናቱ እቅፍ በእናቱ ጡት አደገ።

ታዲያ ይህች ብልህ እናት ልጇን ስለ እግዚአብሔር ፍቃድና ስለ ሕዝቧ እያስተማረች እንዳሳደገችው ከሙሴ መረዳት እንችላለን። ያንን ሁሉ ክብር ንቆ ለወገኖቹ መቆርቆሩ እና መሰደድ መምረጡ የእግዚአብሔር አላማ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሙሴ ለዚህ መብቃት የእናቱ ትልቅ አስተዋጽኦ አለበት። ዛሬ እኛስ በባዕድ ምድር ልጆቻችንን እንዴት እያሳደግናቸው ይሆን? በእርግጥ በዚህ ዘመን የሥጋ ባርነት ችግር የለብንም ሆኖም በልጆቻችን ላይ በከፋ ያጠለለ የኃጢያት ባርነት አለ። ወደ ዘለአለም ሞት የሚነዳ ከዚህ እንዴት ይሆን የምናስመልጣቸው? ለልጅ በበጎ ማደግ እናት ትልቁን ሥፍራ ትይዛለች። ዕብ 11፡24-26 ሙሴም ካደገ በኋላ የፈርኦን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ ከግብጽ ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍን እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት እንዲሆን አስቧልና በማለት ይነግረናል።

ቀጣዩ ወደ ገጽ ...7 ዞሯል...

# *ዝም-በሉ*

*........ካለፈው የቀጠለ...አንድ አስደንጋጭ ነገር አዩ ዮርዳኖስ ሲከፈል ማመን አቃታቸው በአጠገቡ ኤልያስ የለም ጉዱን እናያለን ያሉት ሁሉ ኤልሳእ በእጥፍ መንፈስ ዮርዳኖስን በመክፈል ሲገለጥ ተመለከቱ፡ አሁን ሊያፌዙበት አይችሉም አሁን ምን ይውጥሃል ሊሉት አይችሉም ሁለት እጥፍ መንፈስ በላዩ ላይ አለ ወደው ሳይሆን በግድ መተው በእግሩ ስር ወደቁ። 2ኛ ነገ 2፡1-15፤*

*ተቀብቻለሁ፤ ተለይቻለሁ፤ እያለ አልፎከረም አዋጅ አላስነገረም አላቅራራም ግን ማንነቱ በተግባር ታየ በኤልያስ ላይ የነበረው መንፈስ በኤልሳእ ላይ አርፏል አሉ እየተንቀጠቀጡ እጅ ሰጡ መቀባቱን ነብይ መሆኑን እነዚያው የፌዙበት ምን ይውጥሃል ያሉትና ያሙት በአደባባይ በዚያው አፋቸው አዋጅ ተናገሩ በኤልያስ ላይ የነበረው መንፈስ በኤልሳእ ላይ ነው፤ እያሉ። ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሁን፤ እንደተመኘው ጌታ አደረገለት።*

*መጽሐፍ ቅዱስ ስታጠኑ በኤልሳእ የተደረገው ታምራት በኤልያስ ከተደረገው ሁለት እጥፍ ሆኖ ታገኛላችሁ ዘመኑን ሁሉ በብዙ ሞገስ ያገለገለ የእግዚአብሔር ባርያ ሆኖ በክብር አንቀላፋ እግዚአብሒር በበድኑ (በሬሳው) ሳይቀር ታምራት አደረገ፤ ጸንቶ እስከ ፍጻሜ በመንዝ እግዚአብሔር በሕይወት ዘመኑ ሊሰራ ያለውን ሁሉ በብዙ ድል ያከናወነ የእግዚአብሔር ሰው ሆኖ አለፈ። 2ኛ ነገስ 13፡20-21፤*

*ታዲያ ወገኖች የኤልሳእ ሕይወት ለብዙዎቻችን ጥሩ የሕይወት ተሞክሮ ሊሆነን ይችላል የዓላማ ጽናቱ እስከ ፍጻሜ በቆራጥነት መጓዙ። ውድ ወንድሜ አንተ እውነተኛ ባለእራይ አንተ መለኮታዊ ጥሪ ያለ በእርግጥ የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምተህ የወጣህ በምን ውስጥ አለህ? ምን እየተባልክ ነው? ሁሉ ከፍቶብሃል? ነገሮች ግራ አጋብተውሃል? አይዞህ ጸንተህ ቁም የጠራህ ጌታ  በቀኝህ አለ። ጳውሎስ ማእበሉ ወጀቡ በበዛበት ሰዓት ወደፊት እንድናለን የሚል ተስፋ በተቆረጠበት ጊዜ የጌታ መላእክ በዚህ ሌሊት በቀኜ ቆሞ አበረታኝ አትፍራ በቄሳር ፊት ልትቆም ይገባሃል ብሎ አጽናናኝ እያለ ይናገራል። ሐዋ 27፡24                    በዚህ ክፍል እንደምናየው ጳውሎስ በቄሳር ፊት ይቆም ዘንድ ግድ ነው። ስለዚህ ማእበል ወጀብ ቢበዛ የተባለው ቦታ መድረስ አይቀርም፤* ***ታያለህ ወንድሜ በአንተም ላይ የቱንም ያህል መከራው ቢጠነክር ጌታ የተናገረህን እስኪያወርስህ ድረስ አይተውህም አይጥልህም*** *ቃሉም እንደሚል ባለራእይ ራእዩ ሳይፈጸም አይሞትም፤ እንዲያውም በስተመጨረሻው ይቸኩላል ሊመጣ ያለው ይመጣል አይዘገይም ተብሎ እንደተጻፈ አንድ ነገር አስተውል ኤልሳእን ወደ ኋላ ሊመልሰው የሚችል ነገር ይናገሩት የነበሩት ተራ ሰዎች እንዳልነበሩ እንደውም እውነቱን ስናይ አንደኛው ነብዩ ኤልያስ ነው ከአንዴም ሶስቴ ትቶት ሊሄድ በዚህ ቆየኝ እያለ ያስቸግረው የነበረው። ለምን እንደዛ ይለው እንደነበር ግልጽ ማስረጃ የለም ግን ልቡን ሊያሳዝን ተስፋ ሊያስቆርጥ የሚችል ንግግር ይናገረው ነበር በእርሱ እግር እንደሚተካ ያውቃል በዚያ ሊተወው ለምን እንዳሰበ ያስገርመኛል በዚህ ቆየኝ ይለው ነበር። ለምን? ይህ ለእኔም ስላልገባኝ ትቼዋለሁ አሁን ግን ማስተላለፍ የምፈልገው መልእክት ይህ ነው ትልልቅ የምትላቸው የእግዚአብሔር ሰዎች ተስፋ የሚያስቆርጥ ወደ ኋላ የሚመልስ ነገር ሊናገሩህ ይችላሉ አይድነቅህ ዋናው ቁም ነገር የሰማኸው ጥሪ መለኮታዊ መሆኑን ማረጋገጥህ ነው። በእርግጥ አለ ጳውሎስ ለሰማሁት ድምጽ ከደምና ከሥጋ ጋር አልተማከርኩም ስለዚህ*

ወንድሜ ያበረታቱኛል ይደግፉኛ ያልካቸው ሰዎች እንዳልጠበካቸው ሆነው ልታገኛቸው ትችላለህ። አይዞህ በአንተ አልተጀመረም ከላይ እንዳየነው ኤልያስ ኤልሳእን ሊያበረታታው ይገባ ነበር። ነገር ግን ምንም ሲለው አናይም ይልቅ እዚህ ቆየኝ እያለ ጥሎት ሊሄድ ሲሞክር ነው ተጽፎ ያገኘነው ታላቁ ነብይ ኤልያስ እነዚያም የነብያት ልጆች በዚያች የመጨረሻ ሰዓት ላይ የኤልሳእን ልብ የሚያሳዝን ንግግር ቢናገሩትም ከአላማው ፈቀቅ ሊያደርጉት ግን አልቻሉም። ዛሬም ከብዙ ሺህ አመታት ወዲህ ባለው ዘመን ውስጥ ምናልባት ያ ታሪክ በአንተ ላይ ተደግሞ ሊሆን ይችላል ግን ለሰማኸው እውነት ለተቀበልከው ራእይ ግንባርህን አትጠፍ ጥሪህ ከሰማይ ይሁን እንጂ ጨክን ሁሉን በድል ትወጣለህ የጠራህ ጌታ የታመነ ነውና ዛሬ ላይ ቆመህ የተሰጠህን የተስፋ ቃል አሻቅበህ እይ እሱ ለመንገድህ ጉልበት ይሆንልሃል። ጴጥሮስ ጌታን በውሃ ላይ ሲሄድ አይቶት እኔንም እዘዘኝ አለው ጌታም ና ባለው ጊዜ እጅግ ባስጨነቀው ማእበል ላይ እየተጫማው ሄደ ነገር ግን ብዙ ሳይጓዝ አይኑን ከጌታ ላይ አንስቶ ማእበል ወጀቡን ሲያይ መስጠም ጀመረ ማቴ 14፡28-42 ዓይንህን ከጌታ ላይ አታንሳ ማእበል ወጀቡን አትይ ትሰጥማለህ የቱንም ያህል ፈተናው ይበርታ ጌታህን ብቻ እያየህ ጉዞህን ቀጥል ጆሮህን ለአምላክ ብቻ ስጥ።

ኤልሳእን ስናየው ኤልያስ ቢሆን የነብያት ልጆች ቢሆኑ ማናቸውንም ሊሰማቸው ፍቃደኛ አልነበረም። ለምን ቢባል **ያኔ በእርሻው ሥፍራ እያለ መጎናጸፊያውን ሲጥልበት በሬውን ሞፈር ቀንበሩን ያስጣለው መለኮታዊ ጥሪ ከፍ ብሎ በፊቱ ተሰሏአልና፤** ስለዚህ ከጉዞው ሊያስቀሩት አልቻሉም ወንድሜ የትኛውም የሰዎች ወሬ ትጥቅህን አያስፈታ። መለኮታዊ ጥሪ አይደል ያለህ በቃ ወደቀኝ ወደግራ አትበል ፊት ለፊት ጌታህን እይ እሱ ጨክኖ መከራን በመቀበል ድል እንዳደረገ በቆራጥነት ተጓዝ የእብራዊያን ፀሐፊ ስለ እምነት ጀግኖች ሲናገር ስለነ አብረሃም፤ ሙሴ፤ ጌዲዮን፤ ዳዊት ስለሌሎችም በእምነትና በጽናት ነገሥታትን ሳይቀር እንዴት ድል እንደነሱ በምእራፍ አሥራ አንድ ላይ በዝርዝር ከተናገረ በኋላ ወደ ምእራፍ አስራ ሁለት ሲገባ እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢያት አስወግደን የእምነታችንን እራስና ፈጻሚ ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትእግስት እንሩጥ እያለ ይመክረናል። እብ 12፡12፤

ጌታ ለክፉ ቀን ሸሽጎ ያስቀመጠህ ውድ የእግዚአብሔር ባሪያ አይዞህ በአደባባይ ማንነትህ ሊታይና በሁለት እጥፍ መንፈስ ልትገለጥ ቀኑ ደርሷል ስለዚህ ሁሉን ታገስ ሁሉም ደግሞ ዝም በሉ እያልካቸው ወደ ራእይ ፍጻሜ ተጓዝ በለሱን የጠበቀ ፍሬዋን ይበላል ጌታውን የጠበቀ ይከብራል እንደሚል የእግዚአብሔር ቃል አሁንም ቢሆን የከበዱብህን ሰዎች ግራ ያጋቡህን ሁሉ ነገ እግዚአብሔር በእጅህ አሳልፎ ይሰጥሃል፤ ስለዚህ ታገሳቸው ከአፍህ ክፉ ቃል አይውጣ የጠራኝን ጌታ አውቀዋለው ፤ እናንተ **ዝም በሉ** እያልክ ወደፊት ተጓዝ ጌታ በነገር ሁሉ ከአንተ ጋር ይቆማል ፍጻሜህም ያማረ ይሆናል እንዲሁም እህቴ አበቃሁ ሁላችንን ጌታ እግዚያብሔር እስከፍፃሜው ፀንተን በመቆም የተባለልንን የምንወርስ ያድርገን አሜን!!!

ከሂኖክ ተሾመ



*ከገጽ 4 የዞረ....ከሴቶች ለሴቶች*

*እውነት ነው ይህቺ ጠንካራ ሴት ስትወልድ ጀምሮ የነበራት ጽኑ እምነት ልጇም ካሕዛብ ሳይደባለቅ ነጥሮ እንዲወጣ በእምነት እግዚአብሔርንእንዲያይ አስችሎታል እግዚአብሔርም እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነፃ ለማውጣት ተጠቅሞበታል።ታዲያ ወገኖቼ እኛስ ዛሬ ከዚህ ምን እንማራለን ትንሽ ትልቁ እያስፈራራን በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት አስጥሎን ይሆንን? በተለይም ወላጆች (እናቶች) በልጆቻችን ሕይወት ላይ ያለን ድርሻ ታላቅ መሆኑ የታወቀ ነው በምንኖርበት በዚች ምድር በአሜሪካ ጊዜው የማይበቃው ሥልጣኔና ክርስትና አብሮ ለመንዝ የሚያስቸግሩበት ነው በዚሁ ሁሉ ውስጥ ልጆቻችንንም በዙሪያቸው ሥልጣኔ ከሚመስሉ ፈርኦኖች መሙጫ መንገዱን ልናሳያቸው ብርታት ልንሆናቸው ብዙ እጅግ ብዙ ይጠበቅብናል።ጌታ የሰጠንን ጥቂቷን ጥበብ ብንጠቀም በእምነት ብንራመድ በእነ ሙሴ ዘመን የነበረ የእግዚአብሔር ክንድ ልጆቻችንን ከኃጢአት ባርነት ቀንበር ፈልሰው ወደ ክርስቶስ መንግሥት እንዲገቡና የእግዚአብሔር መጠቀሚያ የአላማው መፈጸሚያ ሙሴዎችን ማፍራት እንችላለን እግዚአብሔር ጥበቡና ፀጋውን ይስጠን አሜን።*

**በዮብዳር ፍሰሐ**

## *የመንገድ ሥንቅ ፤*

****የእግዚአብሔር ክብር ማየት ትፈልጋለህ ክብርህን ጣል !*

****የእግዚአብሔርመንግሥት በመሸነፍ ያሸነፈች በተሸናፊዎች የምታሸንፍ ናት! **ዓለምን ለማሸነፍ አትታገል ለእግዚአብሔር ተሸንፍ ዓለምን ታሸንፋለህ!*

***ሁልጊዜ ንቁ ሁን በአንተ እና በጠላትህ መካከል የማይበርድ የጦር አውድማ አለና !*

***ዛሬ አመስግን ነገም አመስግን ከነገወድያም አመስግን ለጥቆም አመስግን ሁልጊዜ አመስግን ያኔ ባለድል ነህ ብታጉረመርም ግን ሽንፈት ከፊትህ ናት! **የመንፈሳዊ ሰው የመንገድ ጉልበቱ ተስፋው ነው በፀሎት ካጀባት በድል ይፈጽማል!*

***ሄኖክ ተሾመ***

## *አይኖቹም አዩና ...*

*ግርማ ሞገስን*
*በጎ ቸርነትን*
*ፍጹም ታማኝነትን*
*አሉ አዎን አዎን*
*ወግ ማእረግ መጣልን*
*ተሳካልን ሆነልን*

*ጆሮቹም ሰሙ ያንተ አፍ ሲናገር*
*ከዘመናት በፊት ያረከውን ታአምር*
*ግሩም ግሩም ተሳካ ተሳካ ምስጥር ምስጥር*
*አሉ በተራቸው እያነቡ ክብር ለእግዚአብሔር*
*ክብር በሰማይ ክብር በምድር ለእግዚአብሔር*
*ስታሻግረኝ የውጣውረድ አባይ*
*ስትደግፈኝ በፈራሁት ጎዳና ላይ*
*ስትመራኝ ወደድል አደባባይ*
*አመኑ ተረዱ እንደሆንክ የበላይ*

*ተገናዘቡ ፈዋሽ እንደሆንክ*
*አመኑ እንደሚያዋጣቸው መንበርክክ*
*ጀመሩ በሞት አደባባይ ወደአንተ ማየት*
*ተሰማሩ አንተን በማመን ያለፍርሃት*
*አስተጋቡ ለጆሮ የመገዛት ትምህርት*
*አመኑ አሜን አሉ ከልብም ጋር በአንድነት፤*

*ከደመቀ*

## ስሜ አልለይሽም !

ታሪክሽን አውቃለሁ እንዴት እንደመጣሽ
በችግር መከራ ከአገርሽ እንደወጣሽ
ባልና ልጆችሽ ዙሪያሽን ከበውሽ
ወደ ሞአብ ምድር ያኔ እንደተሰደድሽ
መራር ቢሆንብሽ የሞአብ ቆይታሽ
ባልና ልጆችሽን ማጣት ግድ ቢልሽ
በቃሽ አትተክዢ እኔ እኮ አለሁልሽ
ልክ እንደልጅ ሆኜ የምኖር ከጎንሽ

ጉዳትሽ ገብቶኛል እኔንም ነክቶኛል
ባሌን በማጣቴም ውስጤ ተረብሿል
ካንቺ ጋርም አብረን ብዙ አመት ኖረናል
ሀዘንን መከራን ሁሉንም አይተናል
በጎውን ብትሰሚ አሁንም ስለሀገርሽ
እንዴት እኔን ትተሽ መመለስን መረጥሽ?
ህዝቤንና አምላኬን ጥዬ እመጣለሁ
ሕዝብሽ ሕዝቤ አምላክሽ አ ሲሆን

አየዋለሁ ለእኔም ማእረጌ
ይህንንም ብላት ግድ አለችኝ እሷ
ስሚያት እንድመለስ ውትወታዋ በዛ
በሆዴ ልጅ የለም ላንቺ ባል የሚሆን
ሆኖም እንኳን ብወልድ ላንቺ ባል አይሆንም
እባክሽ ተመለሽ እኔ አላዋጣሽም
እያለች ምራቴ ብዙ አስቸገረችኝ
እኔም ከሷ በላይ በልቤ ጨከንኩኝ
ይህም ሁሉ አልፎ ተጓዝን በጋራ
ቤተልሄም ገባው እኔም ከሳ ጋራ

ኑሮ ተጀመረ ሀ ተባለ ዳዴ
ምራቴን ለመጠር ቆርጦ ወጥቷል ሆዴ
አልከበደም ኑሮው እኛ እንዳሰብነው
ተሳካልን ፍጹም ነገሩ ከላይነው

እስቲ ላጫውታችሁ ጌታ ያረገውን
በቤትልሔም ሣለሁ ያኔ እህል ሲቃርም
በዛ በሃያል ሰው በቦኤዝ ስታሰብ
ወደ ሌላ እርሻ ከቶ እንዳልላወስ
ፊቱን እያበራልኝ ደግሞ እንድመለስ
እንደ ባርያው ልሆን ገብቼ ከእርሻው
አጽናናኝ በቃሉ ልቤን ደስ አሰኘው
ልታዘዝ ወጥቼ ታዛዥ ተላከልኝ
መስፈሪያዬ ሞላ ቅንጣት ሳይጎድልብኝ
ኧረ ይህን ክብር ከየት አገኘሁኝ
ይህም መች ሆኖ በራሴ በመልክ በውበቴ
ሞገስ ሰጥቶኝ እንጂ ታማኙ ረዳቴ
መስሎኝ ነበር ያኔ በፍቅርሽ ተስቤ የመጣሁ

ካንቺ መለየቱን ፍጹም ስላልፈለግሁ
መች እሱ ሆኖ ምስጢሩ
አሁንማ ገባኝ ምክንያቱ
በሚያይ በሚሰማው ደግሞ በሚመልሰው
በአምላክሽ እኮ እኔ ታስቤ ነው

የወሰንኩትናአምላክሽ አምላኬ ይሻለኛል ያልኩት
አውቆ እኮ ነው እርሱ ልቤን እንደጣልኩበት
በውኑ ተረድቶ እሱን እንዳሻሁት
አምኜው ወጥቼ መቼ ተዋረድኩኝ
በክብር ላይ ክብር ለእኔ ጨመረልኝ
የገባኝ ፍቅሩ ነው ቀዬን ያስለቀቀኝ
ሕዝቤንና አምላኬን ሁሉንም ያስጣለኝ
ስሜ አልለይሽም እመጣለው ያስባለኝ
ይኸው አምላክሽ ነው ባንቺ ውስጥ የታየኝ
በፊት አታውቀኝም ብሎ እኔን ሳይንቀኝ
እንግዲህ እንዳውቀው እድሉን ከሰጠኝ
በሰው ሃገር ሆኜ ሞገስ ከሞላብኝ
ከዘረ ብሩካን ጋር ከቀላቀለኝ ታድያ ምን እላለሁ
ለአማልክት አምላክ ሁሌም እገዛለሁ
. ከሣባ ተስፋዬ

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በቦስተን
ETHIOPIAN EVANGELICAL CHURCH BOSTON
88 TREMONT STREET, BOSTON, MA, 02108
T: 617-523-5058 F: 617-523-5058
www.eecBoston.org